# ልትድን ትወዳለህን ?

## ታውቀውና ትፈጽመው ዘንድ የሚገባህ እንደ ሚከተለው ነው ።

«መዳን በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና ።» የሐዋርያት ሥራ ፬ ፥ ፲፪ ።

ከመንፈስ ጭንቀት ፥ ከርኩሳን መናፍስት መውጊያዎች ፥ ከደዌ ሁሉና ከዘላለም ሞት ማለትም ከገሃነመ እሳት ለመዳን ትፈልጋለህን ?

እነሆ የዓለምን ኃጢአትና ሥቃይ ፥ በሽታም ለመደምሰስ ፥ የመንፈስን ሰላምና የዘላለምን ሕይወት እንዲያው ለመስጠት የመጣው የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደኔ ኑ ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ ፥ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ፥ ከእኔም ተማሩ ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ፥ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ ፥ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና» እያለ ወደ እቅፉ ይጠራሃል ። ማቴ ፲፩ ፥ ፳፰—፴ ። ዮሐ ፡ ፩ ፥ ፳፱ ።

ክርስቶስ ክፉ ከሆነው ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ ሞተ ፥ እንደተቀበረና እንደተነሣ ብታምን ከተጨነቅህበት የሞት መንገድ አሁን ሊያወጣህ የተዘጋጀ የዓለም ብርሃን ነው ። ክርስቶስ የሕይወት ብርሃንና የሕይወት መንገድ ስለሆነ ከምትጓዝበት የጨለማ ጉዞ መልሶ በሕይወት መንገድ ሊመራህ ዝግጁ ነው ።

## እውነትን ብታውቅ እውነት አርነት ያወጣሃል ። «እውነት ምንድነው ?» ትል ይሆናል ።

እውነት ክርስቶስ ነው ። እውነት የሆነው ክርስቶስ እኔንና አንተን የሞት መርገም ከተሸከመው ፈራሽ ሰውነት ፍጹም ወደሆነው ወደ ሁለተኛው አዳም ማለት ወደ ራሱ ወደ ክርስቶስ በዳግም ልደት አሠራር ይሰውጠን ዘንድ በማይበሰብስና በማይፈርስ (በሕያው) ሥጋ ተገለጠ ። በመስቀል ተሰቅሎ በመሞት ሞትንና ሲኦልን ሻረ ። የሞትና የሲኦል መክፈቻም በእጁ ነው ። ራእይ ፩ ፥ ፲፯—፲፰

ከመጀመሪያው አዳም የወረስነው ይህ ደካማው አሮጌው ሥጋ የሰማይን መንግሥት ሊወርስ እንደማይችል ስለሚያውቅ እግዚአብሔር ሰማያዊ አዳም ሆኖ በሥጋ ተገለጠ ። እናንተ ደካሞች ወደኔ ኑ ፤ እኔ ከድካማችሁ አሳርፋችኋለሁ ፤ ከሥጋዊ ሕይወት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት አሻግራችኋለሁ አለን ። ማቴ ፲፩ ፥ ፳፰ ። ፩ኛ ቆሮ ፲፭ ፥ ፵፰—፶ ።

እነሆ የመለወጥ ቀን አሁን ነው ። ዳግም የመወለድ ቀን አሁን ነው ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ወይም ከቀን በኋላም አይደለም ። ከድካምህ ፤ ከሚያስጨንቅህም



ከዚህ ከማይረካው አዳማዊ ሕይወት ሰላምና እረፍት ወደምታገኝበት ወደ ሁለተኛው አዳም ወደ ክርስቶስ ተለወጥና ክርስቶስን በመምሰል በሕይወት ኑር ።

## «ክርስቶስን ለመምሰል እንዴት እችላለሁ ?» ትል ይሆናል ።

«ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአወሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» የሚለውን መለኮታዊ አዋጅ እንመርምር ። ዮሐ ፫ ፥ ፭ ። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፤ ይህም ማለት ከአዳም ዘር የተወለደ አዳማዊ ነው ፤ አፈር ነውና ወደ አፈር ይመለሳል ማለት ነው ። ሥጋና ደም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይሉችም ፤ የሚበሰብ ሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም ተብሎ ተጽፎአል ። ፩ኛ ቆሮ ፲፭ ፥ ፶ ።

ክርስቶስ ግን ሰውም መንፈስም ነው ። ፪ኛ ቆሮ ፫ ፥ ፲፯ ሰውነቱም የማይበሰብስ ፥ መቃብርን ድል ነሥቶ በዘላለም ሕይወት የተነሣ የአምላክ ሥጋ ነው ። ስለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን ምሰሉ ፥ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፥ ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው ያለው ። አንተም ክርስቶስን ለመምሰል ከውኃና ከመንፈስ መወለድ አለብህ ። ዮሐ ፫ ፥ ፭—፯ ።

## «የክርስቶስን ሥጋ እንዴት እለብሳለሁ ?» ትል ይሆናል ።

መጽሐፍ ቅዱስ ፡— «ንስሐ ግቡ ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ፥ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ ። ይህ የተስፋ ቃል ለእናንተ ፥ ለልጆቻችሁ ፥ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና »አላቸው ይላል ። የሐዋ ሥራ ፪ ፥ ፴፰—፴፱ ።

በስሙ በመጠመቅ ከእርሱ ከክርስቶስ እንደምንወለድ ከዚህ በላይ የተጻፈው ጥቅስ ያመለክታል ። በኢየሱስ ስም የተጠመቁት ሁሉ ክርስቶስን እንደለበሱ ቃሉ ሲያብራራ እንዲህ ይላል ፥— «እናንተ ሁላችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና ፥ በክርስቶስ ሃይማኖት እላንትም ሁላችሁ በክርስቶስ የተጠመቃችሁ ክርስቶስን ለበሳችሁ» ። ገላ ፫ ፥ ፳፮—፳፯ ። ደግሞም ቲቶ ፫ ፥ ፭ «እንደ ምሕረቱ መጠን ፥—

ሀ/ ለአዲስ ልደት በሚሆን መታጠብና

ለ/ በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አዳነን እንጂ

እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም » ይላል ።

ባጭሩ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች ለመረዳት የምትችለው አዲስ ልደትን በማግኘት ከአዳም ዘር እንዴት እንደምትላይና በአዲሱ አዳም ማለት በክርስቶስ ሥጋ ውስጥ ለዘለዓለም እንዴት እንደምትኖር ነው ።



በኢየሱስ ስም በመጠመቅ አዲሱን አዳም «ክርስቶስን» ስለለበሱት ሰዎች ፥ ጳውሎስ ሲጽፍ ፥— «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ፥ አሮጌው ነገር (አዳማዊ ሥጋ) አልፎአል ፥ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» ይላል ። ፪ኛ ቆሮ ፭ ፥ ፲፯ ።

አንተም ንስሐ ገብተህ ለኃጢአትህ ሥርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጠመቅ ካልለበስከው በቀር አሁን በለበስከው የአዳም ሥጋ ሆነህ የነፍስ እረፍትንና ርካታን ለማግኘት ፈጽሞ አትችልም ። የመንፈስ እረፍት ያስፈልግሃል ። የሚያውክህና የሚያስጨንቅህ ሌላ አይደለም ። ይህ አሁን በላይህ ላይ ያለው ምድራዊ አዳም ምንም ብታጌጠውና ብትንከባከበት ፈጽሞ የማይረካና በቃኝ የማይል ባዕድ ጠላትህ (ማለት የነፍስህ ጠላት) በመሆኑ ከሰይጣን ጋር በመተባበር ነፍስህን ስለሚያውክ ሰላምን ለማግኘት አያስችልህም ። ገላ ፭ ፥ ፲፯—፳፩ ። ፩ኛ ቆሮ ፮ ፥ ፱—፲፩ ።

ከለበስከው ጠፊ አካል ለመዳን አሁን ብትወስን ክርስቶስን (ሕይወትን) ለብሰህ በሰላም መኖር ትችላለህ ።

## በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አለብህ ፤

ለአዲስ ልደት በሚሆን መታጠብ ክርስቶስን ከለበስክ የዘለዓለም ርስት መያዣ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ መቀበል ያስፈልግሃል ።

ለአዲስ ልደት በሚሆን መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አዳነን የሚለውን አስተውለህ አንብበው ። ቲቶ ፫ ፥ ፭ ። ከአሮጌው አዳም ወጥተህ ክርስቶስን የምትለብሰው ለአዲስ ልደት በሚሆን መታጠብ ማለት በስሙ በመጠመቅ ነው ። የሐዋ ሥራ ፳፪ ፥ ፲፮ ። ፩ኛ ቆሮ ፮ ፥ ፱—፲፩ ። ማር ፲፮ ፥ ፲፮ ። የሐዋ ሥራ ፲፱ ፥ ፩—፮ ።

## በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ማለትስ ምን ማለት ነው ?

አዳም ሲፈጠር በመንፈስ ነበር የተፈጠረው ። ኢዮብ ፴፪ ፥ ፰ ። ፴፫ ፥ ፬ ። ዘፍ ፪ ፥ ፯ ተመልከት ። ነገር ግን አዳም የእግዚአብሔርን መንፈስ ስላረከሰ እግዚአብሔር እንደገና መንፈሱን በመስጠት የአዳምን ነፍስ ለማደስ ፈቀደ ።

አንተም የማይሞት ነፍስና የሚሞት አካል (ሥጋ) ያለህ ሰው ስለሆንክ የሚሞተው ሥጋህ ተሽሮ ወደ ማይሞት የክርስቶስ ሥጋ ስትለወጥ ፥ ነፍስህ ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ መታደስ ይኖርባታል ። ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አስፈላጊነቱ ለነፍስህ መታደስ ነው ማለት ነው ። በመንፈስ ቅዱስ ካልታደስህ በቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት አትችልም ።

# መንፈሱን እንዴት አገኛለሁ ? ትል ይሆናል ።

እግዚአብሔር መንፈሱን ለሥጋ ለባሽ ሁሉ ያለ አድልዎ እንደሚሰጥ በኢዮኤል ፪ ፥ ፳፰ ። በሐዋ ሥራ ፪ ፥ ፩ – ፬ ። በዮሐ ፯ ፥ ፴፯ – ፴፱ ለመመልከት ትችላለህ ። ቃሉ እንዲህ ይላል ፡— «በዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን (የጴንጠቆስጤ ቀን) በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ፡ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው ። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው ፥ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው ። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር» ይላል ። በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት በሌላ ልሳን መናገር ለአንተም ጭምር የተፈቀደ ነው ። የሐዋ. ፪ ፥ ፲፯ – ፳፩ ። ማር. ፲፮ ፥ ፲፯

በማቴዎስ ፫ ፥ ፲፩ እንደተገለጸው በመንፈስ ቅዱስ አጥማቂው ኢየሱስ ስለሆነ ፊትን ዓይቶ የማያደላ የልብ አምላክ ነውና ለቀደሙት ሁሉ እንደሰጠ እንደ ጸጋው ብዛት መንፈሱን ያፈስልሃል ። ስለዚህ መንፈሱን ለመቀበል በመጠማት ልብህን ከፍተህ በጌታ ፊት ተንበርክከህ ብትጸልይ በመንፈስ ቅዱስ ትሞላለህ ። ሕይወትህም ፈጽሞ ይታደሳል ።

ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለድህ ግን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ልትገባ አትችልም ። ዮሐ ፫ ፥ ፭ ።

# ኢየሱስና አብ አንድ ናቸው ።

የተለያየ ዕምነት ያላቸው ሰዎች ኢየሱስ እግዚአብሔር አይደለም ኢየሱስ ፍጡር ሆኖ ተራ ነቢይ ነው ይላሉ ።

ኢየሱስ ራሱን ለደቀመዛሙርቱ ሲያስተዋውቅ ማንነኝ አለ ?

ፊልጶስ አብ ለብቻው በሰማይ የቀረ ሌላ አምላክ መስሎት አብን አሳየንና ይበቃናል ብሎ (ኢየሱስን) በጠየቀ ጊዜ ፡ — ኢየሱስም (አብም) — «አንተ ፊልጶስ ይህን ያህል ዘመን (፴፫ ዓመት) ከስድስት ወር) ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፥ እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?» ብሎታል የዮሐ ፲፬ ፥ ፰ – ፲ ።

በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው» ፥ «እኔና አብ አንድ ነን» የሚሉትን ቃላት በማስተዋል ብት



መለከት ኢየሱስ ራሱ አብ እንደሆነ ለመገንዘብ ትችላለህ ። ዮሐ ፲ ፥ ፴ ፩ኛ ዮሐ ፭ ፥ ፯ ።

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ ፡— ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ፡— ቃል ሥጋ ሆነ» ይላል ። ዮሐ. ፩ ፥ ፩ ፡ ፲፬ ።

ፊተኛይቱ ትዕዛዝ እስራኤል ሆይ ስማ አምላክህ እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው ፥ እርሱንም በፍጹም ልብህ ውደድ የምትል እንደሆነች ተጽፎአል ።

ዘዳ ፮ ፥ ፬ ማር ፲፪ ፥ ፳፱ ።

አምላካችን በአብነት ከዘላለም እንደ አባት የተገለጠ ። ሚል. ፪ ፥ ፲ ።

በወልድነት ደግሞ ሕዝቡን ለማዳን ሥጋን ለብሶ በሰውነት እንደተገለጠ ፤ ማቴ. ፩ ፥ ፳ – ፳፫ ።

በመንፈስ ቅዱስነት ደግሞ ሕዝቡን ለማደስና ለመቀደስ በሶስት መንገድ መገለጹን ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመገንዘብ እንችላለን ። የሐዋ. ፪ ፥ ፩ – ፬ ። ፪ኛ ቆሮ. ፫ ፥ ፲፯ ።

«በምጽአት ጊዜ በምድር ሲነግሥ ሲገለጽም እግዚአብሔር አንድ ስሙም አንድ ይሆናል» ይላል ። ዘካ ፲፬ ፥ ፱ ።

ጳውሎስም «ከሁሉ በላይ የሚሆን፥በሁሉም የሚሠራ ፥ በሁሉም የሚኖር፥አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ» ይላል ። ኤፌ. ፬ ፥ ፮ ።

በሮሜ ፱ ፥ ፭ «ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን» ይላል ።

በቆላስይስ ፪ ፥ ፱ «ደግሞ በእርሱ በክርስቶስ «የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል» ይላል ። እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ ፥ በሥጋ ሞተ ፥ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ ። ፩ኛ ጴጥሮስ ፫ ፥ ፲፰ ። ፩ኛ ጢሞቴዎስ ፪ ፥ ፭ ። ኢሳ ፯ ፥ ፲፬ ። ፱ ፥ ፮

በ፩ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፥ ፲፮ «በእውነትም ታላቅ ነው የአምልኮት ምሥጢር ፡— አምላክ በሥጋ ተገለጠ ፥

በመንፈስ ጸደቀ ፥
ለመላእክት ታየ ፥
በአሕዛብ ተሰበከ ፥
በዓለም ታመነ ፥
በክብር አረገ ወጣ» ይላል ።

እግዚአብሔር አንድ ነው ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ። ፩ኛ ጢሞ ፪ ፥ ፭ ። ጌታህም አምላክህም ኢየሱስ ነውና በእርሱ አምላክነትና ሰው መሆን ብታምን ይበቃሃል ። መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና ። የሐዋ ሥራ ፬ ፥ ፲፪ ።



Apostolische Pfingstgemeinde
Friedelsheimerstr. 18-20
D - 68199 Mannheim (Neckarau) /Germany
Pastor Raymond Wey
Assistent Pastor Sascha Wey
www.jesus-is-god.de

www.jesus-is-god.de

# ልትድን ትወዳለህን ?

Apostolische Pfingstgemeinde
Friedelsheimerstr. 18-20
D - 68199 Mannheim (Neckarau) /
Germany
Pastor Raymond Wey
Assistent Pastor Sascha Wey
www.jesus-is-god.de,
www.v-p-m.de

ለተጨማሪ ማብራሪያ
በፖ. ሣ. ቁ. 4442
አ. አ. ይጠይቁ ።

ተ. ገ.